የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን
Ethiopian Agricultural Authority

# ዜና ሠፅሔት

በሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈፃሚ በየ2 ወሩ የሚወጣ የውስጥ ጋዜጣ

ቅጽ 1 ቁጥር 70 ነሀሴ 2017 ዓ.ም

ርዕይ

በዓለምአቀፍ ደረጃ ዕውቅናና ተቀባይነት ያለው የግብርና ተቆጣጣሪ ተቋም ሆኖ ማየት፤

ተልዕኮ

የግብርና ቴክኖሎጂን፣ አገልግሎቶችን፤ ግብዓቶችና ምርቶችን ጥራት፣ ደህንነት፣ ፍቱንነት፣ፈዋሽነት፣ጤናማነትና ቀልጣፋነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል፤ መልካም ስም ያለውና፣ለአካባቢ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ የቁጥጥር ተቋምና ስርዓት በመገንባትና የግብርና ቁጥጥር ስራዎችን በመተግበር፣ የሀገር ውስጥ እና የአለም ገበያ ተደራሽነትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ለላቀ ሀገራዊ ጥቅምና የኢኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቀትን አስተዋፅኦ ማበርከት

እሴቶች

- ታማኝነት
- ሚስጥር ጠባቂነት
- ቁርጠኝነት
- የህግ የበላይነት
- ተጠያቂነት
- ለደንበኛና ተገልጋይ ትኩረት
- አለማዳላት
- አጋርነት
- ግልጽነት።
- ምላሽ ሰጪነት

አድራሻ፡- ፖ.ሳ.ቁ 31303

ስልክ ቁጥር ፡- 0115534520

የውስጥ መስመር፡- 227/234

ዌብሳይት፡- http:www.eaa.gov.et

ፌስቡክ፡- Ethiopian Agricultural Authority

ቴሌግራም፡-eaapr_1234

## የአሰራር ስርዓቱን በማዘመን ውጤታማ የሆነው የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን
Ethiopian Agricultural Authority

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 12/63 ደንብ ቁጥር 509/2014ዓ.ም የተቋቋመ ባለስልጣን ነው።

የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን፣ የግብርና ቴክኖሎጂ፣ አገልግሎቶችን ግብዓቶችና ምርቶችን ጥራት፣ ደህንነት፣ ፍቱንነት፣ ፈዋሽነት፣ ጤናማነትና ቀልጣፋነትን ማረጋገጥን ተልዕኮ ያደረገ ተቋም ነው። መልካም ስም ያለውና፣ ለአካባቢ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ የቁጥጥር ተቋምና ሥርዓትን በመገንባትና የግብርና ቁጥጥር ሥራዎችን በመተግበር፣ የግብርና ምርቶችን የሀገር ውስጥ እና የዓለም ገበያ ተደራሽነትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ለላቀ ሀገራዊ ጥቅምና የኢኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቅበትን አስተዋፅኦ ማበርከት ተጨማሪ ተልዕኮዎቹ ናቸው።

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በሁለት ዋና ዋና የቁጥጥር ዘርፎች ማለትም በዕጽዋት ቁጥጥር ዘርፍ እና በእንስሳት ቁጥጥር ስር ባሉ ክፍሎቹ የተደራጀና ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ የቁጥጥር ተቋም ሲሆን ከነዚህ ዘርፎች በተጨማሪም የግብርና ሜካናይዜሽን ፣ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጂ ቁጥጥር ስራ ለማስጀመር እየሠራ ይገኛል።

በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የሪጉላቶሪ ስራውን ለማሳለጥና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና ተቀባነት ያለው ተቋም እንዲሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ የአሰራር ስርዓቱን በማዘመንና በማሻሻል ከፍተኛ የሆነ ለውጥ ማስመዝገብ ችሏል፡፡

ይህም ሲባል ሁሉንም አገልግሎቶች በዲጅታላይዜሽን ሲስተም አካቶ እየሰራ መሆኑና የእንስሳት ምርት ጥራትና ግብዓት ምርመራ ማዕከል በ13 አገልግሎቶች ላይ የሰስተኛ ወገን እውቅና በማግኘት አለም አቅፍ ደረጃ የልህቀት ማዕከል እንዲሆን እድል የፈጠረበት ፤ ከዚህ በተጨማሪ ባለስልጣኑ የምሰብ አገልግሎትን በማሳለጥ **‹‹ምርጡ ዲጂታል ግብርና ባለስልጣን››** ሊባል ችሏል።

ወደ ገጽ 2 ዞራል!

ከገጽ 1 የዞረ..

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በ2017 በጀት ዓመት ወደ ውጪ የተላከ ስጋና ተረፈ ስጋ ምርት ከዕቅድ በላይ ማከናወኑን ገለፀ።



የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በ2017 በጀት ዓመት 21200 ቶን ሥጋ እና ተረፈ ስጋ ምርት ወደ ውጭ መላኩን አስታወቀ።

ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀርም ከፍተኛ ብልጫ ማሳየቱ ተገልጿል።

ባለስልጣኑ በቀጣይ አገሪቱ በእንስሳት ምርት ላይ ያላትን ገቢ እንድታሳድግና የንግድ ስርዓቷን እንድታስፋፋ የእንስሳት ምርት ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር ላይ አተኩሮ እንደሚሰራ ገልጿል።

**የወተት ምርትን ጥራትና ደህንነትን ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ስራዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር እየተከናወኑ መሆኑን የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን አስታወቀ።**

የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን ኤስ.ኤን.ቪ ኢትዮጵያ ከተሰኘ መንግስታዊ ካልሆነ ድርጅት ጋር በመተባበር የወተት ምርት ጥራትና ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ በአዳማ አካሂዷል።

በባለሥልጣኑ የእንስሳት ምርት ሬጉላቶሪ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አያሌው ሹመት (ዶ/ር) ለኢዜአ እንደገለፁት የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን በግብርናው ዘርፍ የተጠናከረ የምርት ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት ለመዘርጋት እየሰራ ነው ብለዋል።

በተለይም የወተት ምርት ጥራትና ደህንነት በማስጠበቅ ከዘርፉ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማሳደግ ትኩረት መሰጠቱን ጠቁመዋል።

የወተት አምራቾችን መከታተልና መቆጣጠር አንዱ የባለስልጣኑ ተግባር በመሆኑ በአመራር ሂደት የሚታዩ ክፍተቶችን በመለየት እንዲስተካከሉ ለማድረግ ግንዛቤ እየተፈጠረ መሆኑን አስረድተዋል።

''በሀገራችን የወተት ኢንዱስትሪው ገና በማደግ ላይ ነው'' ያሉት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ ከወተት ምርት ጥራትና ደህንነት ጋር ተያይዞ ያሉትን ክፍተቶች በመሙላት ዘርፉ እንዲያድግ እንደሚሰራም አመልክተዋል።

ህብረተሰቡ ጥራትና ድህንነቱ የተጠበቀ የወተት ምርት እንዲያገኝ ባለስልጣኑ የቁጥጥር ስራዎችን እንደሚያጠናክር አስታውቀዋል።

## ከገፅ 2 የዞረ

በመሆኑም በሁሉም የወተት እሴት ሰንሰለት ላይ የሚገኙ ባለድርሻ አካላት በአግባቡ ሚናቸውን መወጣት እንዲችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መሰጠቱን ገልጸዋል።

በባለሥልጣኑ የወተትና ማር ምርቶች ሬጉላቶሪ ዴስክ ኃላፊ ስምኦን ገብረሚካኤል (ዶ/ር) በበኩላቸው የወተት ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል ከመስራት ጎን ለጎን የወተት ጥራትና ደህንነት ማስጠበቅም ትኩረት ተሰጥቶታል ብለዋል።የወተት ምርት ጥራትና ደህንነት ለማስጠበቅ ለመጀመሪያ ጊዜ በወተት ልማት የተሰማሩ 71 አምራቾች ላይ ከምርት ደህንነትና ጥራት አኳያ ጥናት መካሄዱን ጠቁመው በጥናቱም የጥራት ጉድለት እንዳለ መረጋገጡን ተናግረዋል።በግኝቱ መሠረት የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወስዱ መደረጉንና ባለስልጣኑም ቀጣይነት ያለው ክትትልና ቁጥጥር አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

ከመድረኩ ተሳታፊዎች መካከል በሲዳማ ክልል ወንዶ ገነት ወረዳ በተሻሻሉ የወተት ላሞች እርባታ የተሰማሩት አቶ ሰንበቶ ሙሉ በሰጡት አስተያየት የወተት ምርትና ጥራት ለማስጠበቅ ከመኖ አቅርቦት አንስቶ ወተቱ የሚታለብበት ዕቃ፤ የወተት ምርት የሚቀመጥበት ሁኔታ እና የሚጓጓዝበት መንገድ በጥንቃቄ እንደሚያከናወኑ ተናግረዋል።ለወተት ምርትና ምርታማነት ትኩረት የሚሰጠውን ያህል ለጥራትና ደህንነትም ትኩረት ሰጥቶ መሰራት በዘላቂነት ተጠቃሚ እንደሚያደርግም አስረድተው፤በቀን 180 ሊትር የወተት ምርት በማምረትና ለአካባቢው ገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ መሆናቸውን አመላክተዋል።

PAGE 3

## የእንስሳት መድሃኒት ጥራት ደህነነትና ፈዋሽነነት ማረጋገጥ ላይ በ2017 በጀት ዓመት የተከናወኑ ተግባራት

ጥራት፣ ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ የእንስሳት መድሃኒት በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ 2,850 ቶን ጥራት፣ ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ የእንስሳት መድሃኒት ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ታቅዶ 3,682,967 ቶን የእንስሳት መድኃኒት ጥራት፣ ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል።

ፈጻጸሙም ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ተገልጋዮች አገልግሎቱን ፈልገው በብዛት ባመምጣታቸው ነው።

በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ ለ629 የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን ለማድረግ የታቀደ ሲሆን 559 የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን ተካሂዷል።

በኢንስፔክሽን ወቅትም የታዩት ክፍተቶች መሰረት በማድረግ የተለያዩ እርምጃዎች ተወስደዋል። 7 ድርጅቶች በራሳቸው ፈቃድ ተሰርዘዋል። 25 ድርጅቶች በኢንስፔክሽን ወቅት ክፍተት በመኖሩ እና በሰዓቱ ባለማሳደሳቸው ተሰርዟል። በአንድ አስመጪ የመጠቀሚያ ጊዜ አልፎባቸው የተከማቹ 428 ብልቃጥ ሆርሞን እንዲወገዱ ተደርጓል።

በመግቢያና መውጫያ ኬላ ላይ የጥራት ደረጃቸውን ለማረጋገጥ ለተወሰደ ናሙና ከደረጃ በታች በመሆኑ 30,000 ብልቃጥ አይቨርመክቲን የሚባል የእንስሳት መድኃኒት ተወግዷል። ለተወገዱ መድሃኒቶችም ለሚመለከተው ክፍልም ማረጋገጫ ተጽፏል። 2 ባች በተለያየ ጊዜ ወደ ሀገር ሊገቡ የነበሩ የእንስሳት መድኃኒቶች የመግለጫ ጽሁፍ (labeling) ችግር ስለነበረበት ከኬላ እንዳይለቀቅ ተደርጓል።

## ጤንነቱ፣ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጪ የተላከ የዕፅዋትና የዕፅዋት ውጤቶች በ2017 በጀት አፈፃፀም መልካም ውጤቶች

ጤንነቱ፣ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕጽዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች በ2017 በጀት ዓመት ወደ ውጪ ሀገር ለሚላክ የጥራጥሬ እህሎች የቅባት እህሎች ‘የብርዕ እና አገዳ እህሎች’ የቡና ምርት ‘የአበባ ምርት’ አትክልትና ፍራፍሬ ምርት’ ቅመማ ቅመም ምርት እንዲሁም ሌሎች የግብርና ምርቶች ላይ ተገቢውን ኢንስፔክሽን ወይንም ምርመራ ለማካሄድ 860,000 ቶን ታቅዶ ክንውን 877,750 ቶን (101%) ምርት ወደ ተለያዩ ሀገራት እንዲላክ ተደርጎል።

ይህም ከፍተኛ ክንውን ሲሆን ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ አብላጫ ማምጣቱ ተገልጿል።

ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች ላይ በበጀት ዓመቱ 60.000 ቶን የኢንስፔክሽን ሥራ ለመሥራት ታቅዶ 87.020 ቶን ማከናወን ተችሏል። አፈጻጸም ከፍተኛ መሆን በልዩ ፈቃድ ለቢራ ፋብሪካ የገባው የገብስ ምርት መጠን ከፍተኛ መሆኑ እንዲሁም ቀደም ብሎ በአዳማ በኩል ፍራንኮቫሉታ ተጠቃሚ ሆነናል በሚል የግንዛቤ ክፍተት የጉምሩክ ጽህፈት ቤት መልቀቂያ ሳይጠይቅ ምርቶችን እንዲገቡ ሲያደርግ የነበረው ክፍተት እንዲታረም በመደረጉ ሁሉም የፍራንኮቫሎታ ተጠቃሚ አስመጪዎች ያለ መልቀቂያ ፈቃድ እንዳይገቡ በመከልከላቸውና ሁሉም መልቀቂያ ፈቃድ ወስደው ምርቶች መግባት በመጀመራቸው የመጣ ከፍተኛ ለውጥ ነው::

## የምግብ ደህንነትና ጥራት ላይ የሚታየውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስ የቴክኒክ ቁጥጥር ስርዓቱ ተጠናክሮ በቅንጅት ሊሰራ ይገባል ፡- ሀሚድ ጀማል (ዶ/ር )




በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የእንስሳት ምርት ግብዓት ፣ ጥራት ምርመራ ማዕከል ከግብርና ሚ/ር የአደጋ ስጋትና ቅነሳ እና አካታች የኢኮኖሚ እሴት ማሻሻያ ፕሮጀክት(ድራይቭ) ጋር በመተባበር ለዘርፉ ባለሙያዎች ለሶስት ተከታታይ ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል።

ስልጠናው በምግብ ደህንነት ሬጉላቶሪ አሰራር፣ የባዮሎጂካል እና ኬሚካል ሀዘርድ፣ የፀረ ተባይና መድሃኒት ቅሪት፣ የማይኮቶክሲንና መርዛማ ሚኒራል ብክለት እንዲሁም የእንስሳት መድሀኒት ላብራቶሪ ቁጥጥርና የጥራት ማኔጅመንት ስርዓት አስፈላጊነት ላይ ባለሙያዎች ጠቃሚ ዕውቀት እንዲያገኙ እንዳስቻለቸው እና በተለያዩ ሥራ ክፍሎች ውስጥ የሚሰሩ ባለሞያዎች ልምድና መልካም ተሞክሮ ለመለዋወጥ የሥልጠና ፕሮግራሙ ምቹ ሁኔታ የፈጠረላቸው መሆኑን ገልጸዋል።

ወደ ገፅ 5 ዞሯል

በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የእንስሳት ሪጉላቶሪ ዘርፍ ም/ ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ሀሚድ ጀማል የምግብ ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር ውስጥ አንዱ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ጥቅም ላይ የሚውሉ ኬሚካሎች፣ መዳበሪያ፣ የእንስሳት መድሀኒቶች፣መኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች እንዲሁም ምርጥ ዘር የመሳሰሉ የግብርና ግብዓቶች የጥራት ጉድለት ወይም የአጠቃቀም ችግር በሰው፣ በእንስሳት፣ በዕፅዋትና በምግብ ጥራትና ደህንነት እንዲሁም በንድግና አካባቢ ላይ የሚያስከትሉ አሉታዊ ተፅዕኖ መቀነስ እንዲቻልና ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት ለመገንባት ሁሉም ቴክኒካል ስራ ክፍሎች በቅንጅትና በትብብር መስራት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም የግብርና ቁጥጥር አገልግሎት ሥራዎችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆን ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር በትብብር መሥራት አስፈላጊ መሆኑን በአጽኖት ገልጸው በሥልጠና የተገኘውን ዕውቀት የተሻለ አፈጻጸም ለማስመስገብ ተግባራዊ እንዲደረግ በውይይት ላይ የተነሱ ጠቃሚ ነጥቦች ለምሳሌ የመርዛማ ሚኔራል ብክለት ችግር ለመቅረፍ የእንስሳትና እጽዋት ዘርፍ ቴክኒካል የስራ ኃላፊዎች ከአዲስ አበባ ከተማ ግብርና ቢሮ እና የሞጆ ኬላ ቁጥጥር ባለሙያዎች ጋር ዕቅድ አዘጋጅተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ መልዕክት አስተላልፏል፡፡

በመጨረሻም የእንስሳት ግብዓት ፣ጥራት ምርመራ ማዕከል ኃላፊ ዶ/ር በላቸው ተፈራ የግብርና ግብዓቶች ጥራትና ደህንነት ችግር በምግብ ደህንነትና አቅርቦት ላይ፣ በሰው፣ በእንስሳትና ዕጽዋት ጤና እንዲሁም በአገር ኢኮኖሚና በአካባቢ ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽእኖ ለመቀነስ በየጊዜው የባለሞያዎችን የመፈጸም ብቃትና እውቀት ማሳደግ፣ የሬጉላቶሪ ስታንደርዶችን ተግባራዊ ማድረግ፣ የላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ስርዓት እና ቅንጅታዊ አሰራሮችን ማጠናከር አስፈላጊ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

## በዕፅዋት ዘር ፍተሻ ላብራቶሪ ዓለም አቀፍ እውቅና ለማግኘት እየተሰራ ነው- ም/ ዋና ዳይሬክተር ወንዳለ ሀብታሙ(ዶ/ር )




በኢትዮጵዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን የዕፅዋት ግብዓትና ምርት ምርመራ ላብራቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ ከATI ጋር በመተባበር የሚመለከታቸው የተቋሙ የስራ ህላፊዎች፣ ባለሙያዎች እና ባለድርሻ አካላት በተገኙበት የብሔራዊ የዘር ላቦራቶሪ የጥራት አያያዝ ስርዓት የሰነዶች ማረጋገጫ እና የትውውቅ መድርክ አካሂዷል ፡፡

በአውደ ጥናቱ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የባለስልጣኑ የዕፅዋት ሬጉላቶሪ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ወንዳለ ሀብታሙ ሲሆኑ ፤ የዕፅዋት ዘር ፍተሻ ላብራቶሪ በአለም አቀፉ የዘር ማህበር (InternationalSeedAssociation-ISTA) መስፈርት መሰረት እውቅና ለማግኘት እየተሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ወደ ገፅ 6 ዞሯል

ከ ገፅ 5 የዞረ

ለእውቅና መስፈርቱ እየተከናወኑ ካሉ ስራዎች ዋነኛው የጥራት ትግበራ ስርዓት ሰነዶችን በተለያዩ አለም አቀፍ እና በአለም ዘር ማህበር(ISTA) መስፈርት መሰረት ሰነዶችን ማዘጋጀት ቀዳሚ መሆኑን ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ በISTA አለም አቀፍ እውቅና ያለው የዘር ላቦራቶሪ ለመፍጠርና በአጭር ጊዜ ለማሳካት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሰራ መሆኑንም ተናግረዋል።

በተገልጋዮቹ እና በማህበረሰቡ ዘንድ ታማኝነትን ያተረፈ የግብርና ሬጉላቶሪ ተቋም ለመገንባት ዘርፈ ብዙ ተግባራት እየተከናወነ መሆኑንም ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አመላክተዋል ።

የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢኒስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ፍሬው ተገኝ በበኩላቸው፤እንደ ሀገር ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ ባሻገር ወደ አለም ዓቀፍ ገበያ ለመግባት አለም ዓቀፍ የጥራት መስፈርቶችን ማሟላት ቁልፍ ጉዳይ ነው ብለዋል ።

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በአጭር ጊዜ የተቋቋመ ቢሆንም በሁሉም የቁጥጥር ዘርፎች እያከናዎናቸው ያሉ ተግባራት ሀገርን የሚያሻግር ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ባለስልጣኑ ከተቋቋመ ባጭር ጊዜ ውስጥ የሚሰጥቸውን አገልግሎቶች በሙሉ ዲጂታላዝድ ማድረጉ እና ከ20 በላይ የሚሆኑ የተቋሙ አገልግሎቶች ተመርጠው በመሰብ ማእከል እንድሰጡ መደረጉ ለሌሎች አስተማሪና ተሞክሮ የሚሆን ስራ ነው ብለዋል።

ሀገርን ከፍ የሚያደርግ የግብርና ሬጉላቶሪ ተቋም ለመገንባት ለሚደረገው ርብርብ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢኒስቲትዩት የድርሻውን እንደሚውጣ ዶ/ር ፍሬው ገልፀዋል ።

ብሔራዊ የዘር ላቦራቶሪ የጥራት አያያዝ ስርዓት የሰነዶች ዝግጅት ላለፉት ሶስት ወራት ከተለያዩ የመንግስት እና የምርምር ተቋማት በተውጣጡ ባለሙያዎች 76 የሚሆኑ ሰነዶች ሲዘጋጁ መቆየታቸውን የባለስልጣኑ የዕፅዋት ግብዓትና ምርት ምርመራ ላብራቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ አቶ መለስ አስራት ገልፀዋል።


በመድርኩ ላይ የተዘጋጁ ሰነዶች ፣በሰነድ ዝግጅቱ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች፣ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ነጥቦች፣የባለስልጣኑ የእንስሳት ምርት ግብዓት ጥራት ምርመራ ማዕከል ልምድ ማካፈልን ጨምሮ ተዳሰዋል።

ባለስልጣኑ በእንስሳት ምርት ግብዓት ጥራት ምርመራ ማዕከል በ13 የጥራት ምርመራ አይነቶች ዓለም አቀፍ ዕውቅና ማግኘቱ ይታወሳል።






PAGE 7




# የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት መጠናቀቅ ለኢትዮጵያ ህዝቦች ትልቅ ብስራት ነው።

# ይህ ፕሮጀክት ሁሉም ህዝብ አሻራውን ያስቀመጠበት የድል ውጤት ነው።




**እንኳን ደስ አላችሁ!**

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በ2017 የወጪ ንግድን በማሳለጥ ላስመዘገቡት የላቀ አፈጻጸም ሽልማት ሰጡ።

በ 2017 ዓ.ም የኢትጵያ ግብርና ባለስልጣን ሙሉ በሙሉ ወደ ኢፊቶ የተቀየረ እና ከሌሎች ብሄራዊ ድርጅቶች ጋር የተዋሃደ ብሄራዊ የእንስሳት ጤና አጠባበቅ ስርዓቶችን ጨምሮ 66 አገልግሎቶችን ሙሉ በሙሉ ዲጂታል አድርጓል።

## ቡሄ፣ ጅራፍ፣ ችቦ እና ሙልሙል

═════❖=====

የደብረ ታቦር ወይም የቡሄ በዓል በየዓመቱ ነሐሴ 13 ቀን የሚከበር በዓል ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከምታከብራቸው ዓቢይ (ዋና) በዓላት አንዱ ነው።

### ቡ ሄ

ቡሄ ማለት ‹መላጣ፣ ገላጣ› ማለት ነው። በአገራችን ክረምቱ፣ ጭጋጉ፣ ደመናው ተወግዶ የብርሃን ወገግታ የሚታይበት በዚሁ በዓል አካባቢ ስለ ኾነ በዓሉ ‹ቡሄ› ተብሎ ይጠራል። በዓለ ደብረ ታቦር ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ መለኮቱን የገለጠበት፤ ብርሃን የታየበትና ድምፀ መለኮቱ የተሰማበት ዕለት ስለ ኾነ ‹የብርሃን› ወይም ‹የቡሄ› በዓል ይባላል።

"ቡሄ ከዋለ የለም ክረምት፤

ዶሮ ከጮኸ የለም ሌሊት " እንዲሉ።

በሌላ በኩልም "ቡኮ" /ሊጥ/ ተቦክቶ ዳቦ የሚጋገርበት "ሙልሙል "የሚታደልበት በዓል በመሆኑ ቡሄ ተብሏል።

### ጅ ራ ፍ

በደብረ ታቦር በዓል በትውፊታዊ መልኩ የሚታየው ምስጢር የጌታችን ምስጢራዊ ሞቱ ነው። ጅራፍ መግመድ እና ጅራፍ ማጮኽ ሁለት ዓይነት ምስጢር ይዞ የሚከወን ትውፊታዊ ተግባር ነው። የመጀመሪያው ግርፋቱን እና ሞቱን እናስብበታለን። እንዲሁም ድምፁን ስንሰማ የባሕርይ አባቱን የአብን ምስክርነት ቃል፣ እንደ ነጎድጓድ ድምፅ ያስታውሰናል። የጅራፍን ትውፊታዊነት (ውርስ) መጽሐፋዊ ትምህርትና ምስጢር ጠብቆ ለትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ ጨዋታውን በተራራማ አካባቢ፣ ከመኖሪያ ቤት ርቆና፣ በሜዳ ይደረጋል።

### ች ቦ

ችቦ የጌታችንን ብርሃነ መለኮት መገለጥ የሚያመለክት ነው። በመሆኑም ችቦ ለኩሰን በዓሉን እናከብራለን። የዚህ ትውፊት በብርሃኑ ድምቀት የቀኑን መምሸት ያልተረዱ እረኞች በሜዳ ቀርተዋልና ወላጆች ከመንደር ችቦ ለኩሰው ልጆቻቸውን ፍለጋ ሔደዋልና ታሪኩን እያዘከርን በዓሉት እናከብራለን። የችቦው መንደድም ሌላ ትርጉም አለው። አንድ ምእመን ለሌላው ምእመን መካሪ አስተማሪ መሆኑን፣ መከራ እየተቀበለም አርአያ፣ ምሳሌ፣ ብርሃን መሆኑን ያሳያል።

### ሙ ል ሙ ል

በችቦ ብርሃን ልጆቻቸውን ፍለጋ የወጡ ወላጆች ዳቦ ጋግረው ይዘውላቸው ወጥተዋል። ስጦታው ቤተሰባዊነትን፣ ፍቅርንና መተሳሰብን መግለጫ ነው። ወደ ቤታችን "ቡሄ " እያሉ ለሚመጡ አዳጊዎችም ዘምረው እንዳበቁ የሚሰጥ "ሙልሙል" ዳቦ አለ። … ሕፃናቱም ሊዘምሩ ሲመጡ ዳቦ መስጠት ልማዳዊ ብቻ አይደለም። ሕፃናቱ የደቀ መዛሙርት ምሳሌ ናቸው። መዝሙራቸው ደግሞ ሐዋርያት "የምስራች " ይዘው የመምጣታቸው ምሳሌ ነው። ሐዋርያት በገቡበት አገር አስተምረው አጥምቀው የጸጋ ልጅነትን አሰጥተው በረከት አድለው እንደሚሔዱም፣ ልጆችም ዘምረው፣ አመስግነው፣ መርቀው "ውለዱ ክበዱ፣ ሀብት አግኙ፣ የመንግሥተ ሰማያት ወራሾች ያድርጋችሁ…." ይላሉ።

# ቡርፌ ሕሣሠጁ

## የእሳትና ውሃ በሬ መግዛት

-------------------//------------------

እሳትና ውሃ አብረው አንድ በሬ ገዝተው ነበር ይባላል። ያንንም በሬያቸውን ሌባ ሠርቆ አደረባቸው።

በዚህ ጊዜ አቶ እሳት፡-

"ጌታዬ አቶ ውሃ ካንተ በቀር እኔ ሁሉንም አሸንፋለሁ፤ የሚችለኝ የለም፤ ገንዘቡ እንደሆነ የሁለታችንም ነው። ስለዚህ ተነስቼ ደኑንም፣ ሣሩንም፣ ቤቱንም አቃጥዬ የበሬያችንን ሌባ ልፈልገው" አለው።

ውሃውም፡-

"ወንድሜ አቶ እሳት ምነው እንደዚህ ማለትህ? የሰረቀውንም ደህናውንም አንድ ላይ አድርጎ ማቃጠል ተገቢ ነውን? ሌባችንን ለመያዝ እንደሆነ የሚቸግረን ነገር የለም አሁን እናገኘዋለን።

"እጠብስ ያለ ካንተ፣ አጥብ ያለ ከኔ የሚቀር አለን? በዚያ ጊዜ ልንይዘው ይቻላል" ሲል መለሰለት።

ወዲያው ይህንን ተነጋግረው ጥቂት ሳይቆዩ አንዱ ቅልጥም ይዞ ወደ እሳት መጣ፤ አንደኛው ደግሞ ጨጓራ ሊያጥብ ከውሃ ዘንድ ሄደ። በዚህ ጊዜ ሌቦቹ ስለታወቁ ተያዙና ታሰሩ ይባላል።

መተባበርን ገንዘብ ያደረገ ጠላቱን ያሸንፋል።

## የታላላቅ ሰዎች አባባል

መሪ ማለት መንገድን የሚያውቅ ባወቀበት መንገድ የሚሄድና ለሌላው የሚያሳይ ሰው ነው።

ደካማሰዎችበቀልን ይፈልጋሉ፣ ጠንካራዎቹ ይቅር ይላሉ፣ ምጡቅ ግን እንዳልተፈጠረይተወዋል። (አልበርትኢንስታይል)

 ደግሜ ደግሜ ወድቂያለሁ ለዛ ነው የተሳካልኝ። (ሚካኤልጆርጃን)

 መብረር ካልቻልክ ሩጥ፣ መሮጥ ካልቻልክ ተራመድ፣ መራመድ ባትችል ተንፏቀቅ እንጂ ወደ ፊት መራመድህን አታቅም።

(ማርቲ ሉተር ኪንግ)

